# የውዳሴና የሽብሸባ ጊዜ ነው!

በጁሊ ሜየር (*Julie Meyer*)

**ጉብኝት ከጁሊ ሜየር፥ ጁሊ ሜየር በ"ዓለም አቀፍ የጸሎት ቤት" በካንሳስ ከተማ** (ኢንተርናሽናል ሀውስ ኦፍ ፕሬየር፥ International House of Prayer) **በአምልኮ መሪነት እ.ኤ.አ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ታገለግል ነበረ።**



**ጌታ ወደ እኔ መጣና፥ "*ወዳጆቼን እንድትተዋወቂያቸው እፈልጋለሁ፤*" አለኝ። በጣም ጓጉቼ፥ ኢሳይያስ፣ ኤርሚያስ፣ ጴጥሮስ፣ ዘካሪያስ፣ ሙሴን ለመተዋወቅ እየሄድሁ እንደሆነ አስብ ነበር። እጄን ይዞኝ ወደ ሰማይ እየተሽከረከርን መብረር ጀመርን፥ ካርቱን ፊልሞች ላይ እንዳለ ዙረት። ምንም እንኳን ከምድር በጣም ርቂ ቢሆንም አልፈራሁም ነበር። ዙሪያውን ዝም ብለን እየበረርን ነበር እናም ንፋሱ በጉንጮቼ ላይ ይሰማኝ ነበር። እጁ እጄን እንደያዘኝ ይሰማኝ ነበር እናም ከምድር በጣም ከፍ ብዬ ነበር፥ በፊቴ ላይ የሚነፍሰውን የንፋሱንም ስሜት ወድጄው ነበር። ብቻ እጆቹን ይዤ፥ ምንም አልፈራሁም። ድንገት በቅጽበት ፊቱ ሲቀየር አየሁ። ፊቱን በምድር ላይ አተኮረና ቀጥታ ወደ መሬት መምጣት ጀመርን። ተመለከትሁት፥ ፊቱን አየሁት እናም በዓይኖቹ ውስጥና በፊቱ ላይ ቆራጥነት ይታየኛል። (ኢሳይያስ 50፡7 *ፊቴን እንደ ባልጬት ድንጋይ አድርጌዋለሁ፥*)**


**በእርግጠኝነት ከመሬት ጋር እንጋጭም እያልሁ ማሰላሰሌን ቀጠልሁኝ፥ ነገር ግን ፊቱን ባየሁት ጊዜ ቆርጧል እናም ምንም እንኳን እጁን የያዝሁት ቢሆንም የሆነ ከባድ ፍርሀት መጣብኝ። በጣም በፍጥነት ቁልቁል በአናታችን ወደ መሬት እየበረርን ነበር እናም ግን እርሱ የሚመለስ አይመስልም። በድንገት መሬቱን ጠርምሰን ተላተምን። የግጭቱን ስሜት በአናቴ ውስጥ ተሰማኝ። አክሽን ፊልም እንደማየት ነበር። መሬቱ ሲፈነዳ የነበረው ድምጽ ልክ የህዋ መንኮራኩር (ሮኬት) ወደ ጠፈር ሲመነጠቅ አጠገቡ ቆመው ያለውን ድምጽ ዓይነት ሆኖ ተሰማኝ። የሚያደነቁር ነበር። በመሬት ውስጥ ሰንጥቀን እየሄድን ነበር እናም የጌታ ፊት ፈጽሞ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አይልም፤ ተነጣጥሯል፥ ቀጥታ ፊት ለፊት። ወደ መሬት ስንመጣ፥ ከመሬት ጋር ስንጋጭ፥ እንዲሁም በስተነው ስናልፍ እያንዳንዷን ቅጽበት በዓይኔ ማየት ይቻለኝ ነበር። ምድርን፥ አለቱን፥ ውኃውን፥ የሚነድ እሳት ማየት እችል ነበር፥ እንዲሁም ሰውነቴ ሲቦጫጨቅና ሲቃጠል ይሰማኝ ነበር። ልክ መሬቱና ድንጋዮቹ የእውነት ሰውነቴን የሚቦጫጭቁት ያህል ነበር የሚመስለው ልክ የእውነት እየሆነብኝ እንዳለ። በህልሜ ከባድ ህመም ይሰማኝ ነበር።**

**በድንገት በምድር ውስጥ ሰንጥቀን በሌላኛው በኩል ወጣን። ቆም ብዬ ሰውነቴን ወደታች ተመለከትሁት፥ ተቦጫጭቆ ነበር፥ ቆዳዬ ተገሸላልጧል፥ እናም ህመሙ ይሰማኝ ነበር፥ ነገር ግን ስለእኔ አልነበረም። ኢየሱስ ተመለከተኝ፥ ወደ ፊቴ ተጠግቶ፥ ፊት ለፊት ዓይን ለዓይን፥ እናም እንዲህ አለኝ፦ "*ወዳጆቼን እንድትተዋወቂያቸው እፈልጋለሁ።*" ከህመሜ ብዛት የተነሳ እያለቀስሁ ነበር። በእርግጥ ምን ያህል እንደተጎዳሁና ቆዳዬ ምን ያህል እንደተጎዳ ያስተውለዋል ብዬ እያሰብሁ ነበር፥ ነገር ግን አልተመለከተኝም። ዙሪያውን ተመለከትሁ እናም በሰዎች የተጨናነቀ ቦታ ነበር። ፈጽሞ እዚህ ቦታ መጥቼ አላውቅም፥ ነገር ግን ሕንድ እንደነበረ አወቅሁ። በጣም መጥፎ ሽታ ነበረው እናም ብዙ ሰዎች በየቦታው ይገኛሉ እናም እኔ ጌታን እየተከተልሁት ነበር። እኔን ጭራሽ እየተመለከተኝ አልነበረም። የተገሸላለጠውን የቆዳዬ ህመም እንዲሰማኝ የፈለገ ነው የሚመስለው። በየቦታው ትናንሽ ሕፃናት ነበሩ።**

የሚያማምሩ ሕፃናት ሴት ልጆች በቅርጫቶች ውስጥ ነበሩ እናም **እርሱ** ከእያንዳንዱ ጋር ነበር። በቃ ከእነርሱ ጋር ይቆማል። በዓለም የተረሱ የሚመስሉትን ሰዎች ነበር **ጌታ** ወዳጆቼ ያላቸው። ሕፃናት በመሬት ላይ ተኝተውና ዝንቦች ቆዳቸውን ወረዋቸው አየሁ፥ እናም ከዚህ ዘግናኝ ህይወት ወደሚቀጥለው ህይወት ሲሸጋገሩ አየኋቸው እናም ወደ ዘላለም ሕይወት በሚነቁበት ቅጽበት፥ **እርሱ** በዚያ ነበር፥ ለእያንዳንዳቸው፥ በዚያ ነበር። **አንድስ እንኳን** በ**እርሱ** ዓይን የተረሳ የለም፥ አንዳቸው እንኳን። የማየው ነገር ሀዘን፥ ሰውነቴን ከሚሰማኝ ህመም ጋር ተጨምሮ፥ እንባ በእንባ አደረገኝ። **ጌታ** ወደ እኔ መጣና በፊቴ ትይዩ ቆመ እናም ስለእኔ ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር፥ ህመሜን ያስተውለዋል ብዬ ነበር፥ በዚያ ቅጽበት፥ **እርሱ** ግን እንዲህ አለ፦ "***አሁን በሥጋሽ እንደሆነው ልብሽ ካልተገነጠለና ካልተቀደደ፥ ወዳጆቼን ልታውቂያቸው አትችዪም።*** በእርግጥ ከምቋቋመው በላይ ነበር። እዛው ሆኜ ልጆች ሲሞቱ፥ እናቶች የመጨረሻ እስትንፋሳቸው ሲስቡ፥ በሽታ ሲዛመት እናም ሕፃናት ሴቶች ሲሸጡ እያየሁ ነበር፥ **እርሱም** "***አሁን በሥጋሽ እንደሆነው ልብሽ ካልተገነጠለና ካልተቀደደ፥ ወዳጆቼን ልታውቂያቸው አትችዪም። እኔንም አታውቂኝም፤***" አለ። እናም በእንባ ጎርፍ ስሰጥም፥ ማመን እስኪያቅተኝ፥ በፊቴ ፊትለፊት መጥቶ፥ ዓይን ለዓይን በሹክሹክታ እንዲህ አለ፥ "***የሽብሸባ ጊዜ ነው።*** ልክ የ**እርሱ** የምስጢር መሳሪያው እንደሆነ አድርጎ ነው የተናገረው፥ ሽብሸባውን...



በእግሮቹ ማሽብሸብ ጀመረ፥ እንደወታደር አረጋገጥ (like stomping)። እነዚህ የሞትንና የሕይወትን ጠባሳ የገለጡት ፍጹማን እግሮቹ ይህን ውበት ያለውን ሽብሸባ እያቀረቡ ነበር፥ የነገድ ሽብሸባ -- ኢፍትሀዊነትን የሚረግጥ የ**ጌታ** እግር። ካየኋቸው ሽብሸባዎችና አረጋገጦች ሁሉ ኃያል የሆነ ነበር። **ጌታን** **እርሱ** **እራሱ**፥ በጥልቅ ፍቅር ጠባሳ በወዳጆቹ ላይ በተደረገው ኢፍትሀዊነት ላይ ሲያሸበሽብ ማየት። ደገመው፥ "***አሁን በሥጋሽ እንደሆነው ልብሽ ካልተገነጠለና ካልተቀደደ፥ ወዳጆቼን ልታውቂያቸው አትችዪም። እኔንም አታውቂኝም።***




ከዚያም እጄን ያዘኝና እንደገና ቀጥታ በምድር እንብርት ሰንጥቀን ሄድን እናም አሁንም፥ ቆዳዬና ሥጋዬ ከአጥንቴ ላይ ሲቦጫጨቁና ሲገነጣጠሉ ከባድ ህመም ይሰማኝ ነበር እንዲሁም ምድርን ጠርምሰን ስናልፍ ያለው ያ ነጎድጓዳዊው ድምጽ። በድንገት በሀኪም ቢሮ ቆመን ተገኘን፥ እንደ ክሊኒክ ዓይነት። የመጀመሪያው ሀሳቤ ስለራሴና የነበርሁበት ህመም ነበር። ሰውነቴ ላይ ምንም ቆዳ ያልነበረኝ ያህል ተሰማኝ፥ የተገፈፈ ያህል። እንደገና "***ወዳጆቼን እንድትተዋወቂ እፈልጋለሁ፤***" አለኝ። ዙሪያውን ተመለከትሁና በሕፃናት የተሞላ የቆሻሻ ቅርጫት አየሁ። ጭንቅላቶችና እጆች እንዲሁም ትናንሽ እግሮች በቆሻሻ ቅርጫቶች የተሞሉ ሕፃናት። አንዳንዶቹ በሕይወት ሆነው ይንቀሳቀሱ ነበር፥ ቆዳቸው ተቃጥሏል፥ አንዳንዶቹ ጭንቅላቶቻቸው ተጨፍልቀዋል፥ አንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ የተሟሉ ናቸው፥ ዓይኖቻቸው በግልጹ ተከፍተው እንዳፈጠጡ። ንዝረት ውስጥ እንዳለሁ ዓይነት ተሰማኝ። **ጌታ** ዓይኖቼን በዓይኑ እያየ "***አሁን በሥጋሽ እንደሆነው ልብሽ ካልተገነጠለና ካልተቀደደ፥ ወዳጆቼን ልታውቂያቸው አትችዪም። እነዚህ ወዳጆቼ ናቸው።*** አንድ ሌላ ልጅ እግሩን ተይዞ ወደ ሌላ የቆሻሻ ቅርጫት ሲጣል እዛው ቆሜ ነበር፥ ሙሉ ሕፃን። የ**ጌታ** ሀሳብ ይሰማኝ ነበር።

“*ኦ የምድር ዝምታ፥ የተረሳችሁ የምትመስሉ። አልተረሳችሁም! አልተረሳችሁም! አልተረሳችሁም!*”

**በምድር በዚያች ክፍል ውስጥ ዝም ብለው ነበር፥ ነገር ግን በአብ ፊት የሚሰማ ድምጽ ነበራቸው፥ ሁሉን ቻዩ አምላክ።** ጩኸታቸው በዘላለም መተላለፊያዎች ፈጽሞ አይቋረጥም። ቀንና ማታ፥ ማታና ቀን እየጮኹ አሉ፥ የገነት ተደማጭነት አላቸው። ተደማጭነት አላቸው፥ **የሁሉን ቻይ አምላክ ጆሮ**። መጮኽ ጀመርሁ። “ይህን በከንቱ አታደርጉም፥ ሎ(LOU)። ይህንን በከንቱ አታደርጉም! ሎ ኢንግል!(LOU Engle!) ይህን በከንቱ አታደርጉም፥ ሎ!” በገነት አዳራሾች አልፎ ማየት ይቻለኝ ነበር እናም የሎ መልአክ ስም በገነት የታወቀ ነው። ሎ የጌታን ወዳጆች ያውቃቸዋል። የሕፃናቱ የማያቋርጥ ጩኸት በገነት መተላለፊያዎች ዘለቆ ይሰማኝ ነበር፥ በምድር ድምፅ አልባ የሚመስሉት፥ በምድር የተረሱት፥ ነገር ግን የአብ ጆሮ ወደ እነርሱ ናት እናም ቀንና ለሊት እንዲሁም ለሊትና ቀን በምድር ብርቱህን ላይ ስለፍርድ ይጮኻሉ፥ ነፍሳቸውን ባሳለፏት ላይ ስለፍርድ። ነገር ግን ... በዘላለም ሕይወት ድምፅ አላቸው!!! ሌትና ቀን ቀንና ሌሊት ... በምድር ብርቱህን በሚመስሉት ላይ ስለፍርድ እየጮኹ... እናም የአባታቸው ጆሮ ወደ እነርሱ ናት! እናም በድንጋሚ፥ ጌታ ወደ ዓይኔ ውስጥ እየተመለከተ “***አሁን በሥጋሽ እንደሆነው ልብሽ ካልተገነጠለና ካልተቀደደ፥ ወዳጆቼን ልታውቂያቸው አትችዪም፥እኔንም አታውቂኝም።***”

እየተንሰቀሰቅሁ እዛው ቆሜ ቀረሁ እናም በድንጋሚ ፊትለፊቴ ቆሞ፥ ወደ ዓይኖቼ ተጠግቶ በለሆሳስ “*የሽብሸባ ጊዜ ነው፤*” አለ። ያን የእርሱን “አዲስ ሽብሸባ” ጀመረ፥ የምድርን ኮረብታዎች በደለደሉት በእነዚያ ፍጹማን እግሮቹ፥ አሁን እነዚያ እግሮች እያሸበሸቡና በኃይል እየረገጡ ነበር (stomping by His feets)፥ እዛው ውርጃ የሚፈጸምበት ክሊኒክ ውስጥ። በጣም ኃይለኛ ነበር። ሁልጊዜም በጣም በተሰበርሁበትና በጣም በደከምሁበት ጊዜ ነበር “***የሽብሸባ ጊዜ ነው። የውጊያ ጊዜ ነው፥ ሽብሸባ ውጊያ ነው።***” ይለኝ የነበረው። በእግሩ ይረግጣል፥ በዚህ አዲስ ስልት፥ በዚህ በእግሮቹ አረጋገጥ። ይህ ባለ ሁለት እርምጃው አይደለም፥ ይህ ፈራጁ ኢፍትሀዊነትን ሲረግጥ ነው፥ በገዛ እግሮቹ እናም እንዲህ አለ፡ “***ምድር በዚህ ሽብሸባ እስክትቀላቀለኝ ድረስ ብቻ ጠብቂ፥ ጥቂቶች ተቀላቅለውኛል እናም ግብዣውን እያሰራጨሁ ነው ነገር ግን ልታሸበሽቢ የምትችይው ልብሽ በጣም ሲቀደድና ሲሰበር ነው።***”

ከዚያም በድንጋሚ ወደ እኔ መጣና እንዲህ አለኝ፡ “***አንዳንድ ወዳጆቼን እንድትተዋወቂያቸው እፈልጋለሁ።***” እናም አሁንም በድንጋሚ በምድር ውስጥ ሰንጥቀን አለፍን። ፈጽሞ መቆም አልቻልሁም። ልቤ ተሰብሮ ነበር። ቆዳዬ ተቦጫጭቆ ነበር። ወደታች ስመለከት አጠገቤ ፈንጂ የፈነዳ ነበር የሚመስለው። በጣም በጣም በተጨናነቀ ጎዳና ላይ እየሄድን ነበር። እርሱ ቀድሞኝ ነበር እናም እኔ በጣም በህመም ውስጥ ነበርሁ፥ ቀስ እያለ እንዲራመድ ፈለግሁ፥ ነገር ግን ስለእኔ አልነበረም። ህማሙ እንዲሰማኝ ፈልጓል፥ ምክንያቱም ልቤ ህመሙን እንዲያውቀውና እንዲቀበለው እንደራሴ አድርጌ እንድወስደው ይፈልጋል። አጠገቡ ደርሼ ከእርሱ እኩል እስክራመድ ድረስ ጠበቀኝ። ይህ ቦታ እስራኤል እንደሆነ አወቅሁ። በተለያዩ ጊዜዎች ራሱን ለተለያዩ ሰዎች ጎንበስ ሲያደርግ አየዋለሁ፥ “ሰላም” ወይም “ሻሎም” እንደማለት።



አልተናገረም፥ ራሱን ብቻ ነው ጎንበስ ያደረገው። የዓይናቸውን ትኩረት ይይዝና መልሶ ጎንበስ ይላል እናም ራሱን ጎንበስ ያደረገለትን ሰው አየዋለሁ፥ ዓይናቸው ፍክት ይላል። ውስጣቸውን ተመለከትሁ እናም ብርሃን ሲመላለስ ይታየኝ ነበር። በጨረፍታ ይታየኛል፥ **ኢየሱስ** የልባቸውን ዓይኖች ይከፍታል እናም በግልጽ ያዩታል፥ እንደ **ኢየሱስ፥ መሚሐ**። በዚህ የኢየሩሳሌም ጎዳና እየሄድን በግልጽ ውስጣቸውን ማየት ይቻለኝ ነበር፥ የልባቸው ዓይኖች ተከፈቱና ትንሽ እሳት በውስጣቸው መቀጣጠል ጀመረ።

አንገቱን ጎንበስ ያደረገላቸው ሰዎች ታላቅ ስልጣን ያላቸው እንደሆኑ አወቅሁ፥ በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ አለቆች - ረቢዎች። (ዮሐ.1:39 እነርሱም። ረቢ፥ ወዴት ትኖራለህ? አሉት፤ *ትርጓሜው መምህር ሆይ ማለት ነው።*) **ጌታ** ዓይኖቻቸውን ሲከፍተው በግልጽ ማየት እችል ነበር፤ **ጌታ** ሲገለጥላቸው ይታየኝ ነበር። በምድሪቱ ላሉ ከላይ ያሉ ረቢዎች፥ በጨረፍታና በጉንበሳ ብቻ፥ የመገለጥ ነበልባል በውስታቸው ጥልቀት መቀጣጠል ጀመረ፥ በሰከንድ ውስጥ የልባቸው ዓይኖች ተከፈቱ። (መዝሙር 102:16 *እግዚአብሔር ጽዮንን ይሠራታልና፥ በክብሩም ይገለጣልና።*)

እነዚህን ረቢዎች ቤታቸው ድረስ ተከተልናቸው እናም በቤታቸው የላይኛው ክፍል ገቡ እናም ረቢዎቹ በጉልበታቸው ተንበረከኩና ጮኹ፥ "*ይህ ሁሉንም ነገር ይለውጣል። ይህ ሁሉንም ነገር ይለውጣል።*" **ጌታም** ቀርቦ ትንሿን የመገለጥ ፍም ሲያቀጣጥላትና ቀስ በቀስ ወደማይጠፋ እሳትነት ሲቀጣጠል ማየት እችል ነበር። ይህ ትንሽ የመገለጥ ነበልባል "በአጥንታቸው ውስጥ እንደታመቀ እሳት" ሲሆን ይታየኝ ነበር። ይህ እሳት እነዚህ ረቢዎች ከእንግዲህ ወዲህ አፍነው ሊይዙት የማይችሉበትና ከተራራ ጫፍ ላይ ሆነው የሚጮኹበት ጊዜ እስኪመጣ ሲቀጣጠል አየሁት። *"የሸዋ መሢሑ ነው" … የሸዋ መሢሑ ነው!* (**ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ** ነው!) ካንሳስ ከተማ ውስጥ ባሉ ትናንሽ የጸሎት ህብረቶች ውስጥ ስለዚህ ነገር ጸሎታችንን አስታወስሁ፥ **ኢየሱስ** ይገለጥ ዘንድ፥ በክብሩ ይገለጥ ዘንድ። በእውነትም፥ በእውነትም ተገልጧል።

ዞር አልሁ እናም የ**ኢየሱስ**ን ፊት ሳየው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው እናም እንባ በጉንጮቹ ላይ ይፈሳል እንዲህም ሲል ይሰማኝ ነበር፥ "***ኦ ኢየሩሳሌም፥ ኦ ኢየሩሳሌም።***" ለእስራኤል ያለውን ጥልቅ መውደድና ፍቅር በልቤ ይሰማኝ ነበር። (ማቴዎስ. 23:37 ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም ሆይ፥..ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ!) እናም በምላሹ መልስ ያላገኘው አፍቃሪ ጉዳት ይሰማኝ ነበር፥ ወደ እኔ ተመለከተ፥ አሁንም በድጋሚ፥ "***አሁን በሥጋሽ እንደሆነው ልብሽ ካልተገነጠለና ካልተቀደደ፥ ወዳጆቼን ልታውቂያቸው አትችዪም፥ እኔንም አታውቂኝም።***" በስብእናዬ ጥልቀት ለእስራኤል ያለውን ጥልቅ ፍቅሩ ይሰማኝ ነበር። ልክ ያእቆብ ራሄልን እንደወደዳት፥ ህልቃና ሀናን እንደወደዳት፥ ሆኖም ጥልቅ ፍቅሩ ከተፈጥሮ ፍቅር ያልፋል። አሁንም በድጋሚ ተንሰቅስቄ እያለቀስሁ ነበር እናም የእንባዬ ጨው የሥጋዬን ቁስሎች አቃጠለኝ፥ ሆኖም ግን ማልቀሴን ላቆም አልቻልሁም እናም ከዚህ በላይ ምንም ልቋቋም እንደማልችል በማስብበት ሰዓት፥ እንዲሁም በመሬት ላይ ወላልቄ በወደቅሁበት ሰዓት፥ በሽክሽክታ ደምጽ፥ "***የሽብሸባ ሰዓት ነው፤***" አለኝ።

በድንገት በዋይታ(በለቅሶ) ግንብ ፊትለፊት ነበርን እናም በድጋሚ ጀመረ፥ ይህን አረጋገጡን፥ እየረገጠ፥ ይህን ስልት፥ ይህን ሽብሸባውን በእነዚያ ፍጹማን እግሮቹ፥ ፈጽሞ አይቼው የማላውቀውን። ሁልጊዜም የመጨረሻ ስብራትና ሀዘን በሚሰማኝ ጊዜ ነው፥ "***የሽብሸባ ሰዓት ነው፤***" የሚለው። የኃይሉ ህልውናና የሽብሸባው ኃይል ይሰማኝ ነበር፥ ሽብሸባ በኢፍትህዊነት ላይ። ኦ የሚገርም እይታ የ**እግዚአብሔር ልጅ**ና ፍጹማን እግሮቹ በኢፍትህዊነት ላይ ሲሽከረከሩና ሲያሸበሽቡ። **ኢየሱስ** እየደጋገመ "***የሽብሸባ ሰዓት ነው፤ የሽብሸባ ሰዓት ነው፤***" ይል ነበር። አዲስ የሚመጣ ሽብሸባ አለ፥ ለምድር ድሆች ከአምልኳችንና ከልባችን የሚወጣ፥ የተረሱ ለመሰሉት፥ ነገር ግን **ጌታ** ወዳጆቼ ብሎ የሚጠራቸው እናም ልባችን እስከመጨራሻው ሲሰበር፥ **ያኔ ያኔ** ነው የሽብሸባው ጊዜ። ኦ፥ ምን ዓይነት እይታ ነው የነገሥታት ንጉሥ፥ የምድር ፈራጅና የጥልቅ ፍቅርን ጠባሳ የሚያሳዩ ፍጹማን እግሮቹ፥ ማሽብሸብ ሲጀምሩና ኢፍትህዊነትን ረግጠው ሲያባርሩ። ግልጽ ሽብሸባ ነው። ግልጽ ረገጣ ነው! የሽብሸባ ጊዜ ነው። እናም በህልሜ በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ ስንሄድ፥ እስከ ግንቡ ድረስ፥ ሽብሸባውን የጀመረበት ቦታ፥ ይህንን አወቅሁ፤ በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ በጣም ቁልፍ ለሆኑ ሰዎች፥ በአይሁድ ማህበረሰብ በጣም ለላቁ ረቢዎች በሽብሸባው መሀከል እንኳ **ራሱን** እየገለጠላቸው እንደሆነ አወቅሁ። ዓይኖቻቸው ሲፈኩ አየሁ። ወደ ውስጣቸው አየሁ እናም ልባቸው በኃይል መምታት ሲጀምር። **ጌታ** በውስጣቸው **እርሱና እርሱ** ብቻ ***መሢሑ*** እንደሆነ "ማወቅን" በውስጣቸው ሲያስቀምጥ አየሁ። እንደዚህ ዓይነቱ ሰዓት በላይ ያሉ የተቀቡ የምድር ረቢዎች፥ በ**ጌታ** ጊዜ - ልባቸውን ያነሳሳና ከውስጣቸው ይፈነዳል እናም ወደ ኢየሩሳሌም ከፍታ ስፍራዎች ወጥተው ለመላዋ ኢየሩሳሌም ይጮኻሉ፥ **ያሁሹዋ** መሢሑ ነው። **ያሁሹዋ** ***መሢሑ*** ነው! (**ኢየሱስ** እርሱ **ክርስቶስ** ነው!) (ሐዋርያት.17:3 *ሲተረጉምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ። ይህ እኔ የምሰብክላችሁ **ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ** ነው ይል ነበር።* ማቴ. 1፡16፤ ዮሐ. 17፡3፣ 20፡30፤ ሐዋ. 19፡4)

*በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው።* አሁን፥ ደብቀውት በእርግጥ ሆኖ እንደነበረ ራሳቸውን እየጠየቁ ነው። የተመደበው ሰዓት ተቀርጧል እናም በእነዚህ ጊዜያት አስቀድሞ፥ እየተገለጠ የሰዎችን ልብ ዓይኖች እየከፈተ ነው እናም መጥቶ አጥንታቸው ድረስ ዘልቆ በእሳቱ ያቀጣጥላቸዋል። እነዚህ ረቢዎች የ**ጌታ** ቃል ከውስጣቸው ሲፈነዳ፥ መገለጡንም ሲያውጁ ይታየኝ ነበር። እየሆነ ነው። የተቆረጠው ሰዓት ተቀጥሯል። ዛሬ እየሆነ ነው።

ትንቢተ ኤርምያስ 20፡9 *እኔም። "የእግዚአብሔርን ስም አላነሣም፥ ከእንግዲህ ወዲህም በስሙ አልናገርም" ብል፥ በአጥንቶቼ ውስጥ እንደ ገባ እንደሚነድድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ፤ ደከምሁ፥ መሸከምም አልቻልሁም።*

**ከዛም እንደገና በድጋሚ፥ "*ልክ በሥጋሽ እንደሆነ ልብሽ ሁለት ቦታ ካልተቀደደና ልብሽ ሁለት ቦታ ካልተገነጠለ፥ ወዳጆቼን አታውቂያቸውም፤*" አለኝ።**

# *የሽብሸባ ጊዜ ነው!*

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com